# የክልሎች አውቃቀርና በህገመንግስቱ ላይ የሰፈረው የመገንጠል መብት (አንቀጽ 39) ሲዳሰስ

**ሙሉጌታ ይልማ (ዶ/ር)**

**ስቶክሆልም (January 28, 2018)**

በኢትዮጲያ ሱማሌና በኦሮሞ ክልል መሃል የተፈፀመውን ግጭት ተከትሎ የኢቲዮጵያን ፌዴራላዊ አስተዳደር በጥያቄ ውስጥ የሚያስገቡ ሰዎች ቁጥር ባገር ቤትም ውስጥ ሆነ በውጪ እየጨመረ መጥቷል። በርግጥ በሁለቱ ህዝቦች መሃል ለተፈጸመው ጭፍጨፋና ግጭት የወያኔ ሴራ ከጀርባው መኖሩን የግጭቱ ሰለባ የሆኑ ሰዎችና ሌሎች ታዛቢዎችም በግልጽ የሚናገሩት ጉዳይ እንደሆነ ተደጋግሞ ተገልጿል። ወያኔ እድሜውን ለማራዘምና በስልጣን ላይ ለመቆየት ሲል በኢትዮጲይ ህዝቦች መሃል ግጭት እንዲኖርና በመሃላቸውም ያለው ግኑኝነት እንዲሻክር ያለማቋረጥ ሲሰራበት የነበረ ፖሊሲው ነው። በኢትዮጵያ ሶምሌና በኦሮሞ ህዝቦች መሃል በተከሰተው ግጭት ብቻ ሳይወሰን ባገሪቱ ላይ ለተፈጸሙ የህዝብ እልቂቶችና የህዝብ ግንኙነት መሻከር ምክኒያቱ የወያኔ ከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ውጤት ነው። በአማራው በጋምቤላው በኮንሶው በሶምሌው ላይ ያየነው ጭፍጨፋና የህዝቦች መፈናቀል የሚያረጋግጠውም ይህንኑ ነው። እንግዲህ በመሬት ላይ እንደሚታየው ለችግሮቹ ዋና ምክኒያት የወያኔ የከፋፍለህ ግዛ ፖሊሲ ሆኖ ሳለ፤ ፌደራሊዝምን እንደ ስራአት ጥያቄው ውስት የሚያስገቡና ለግጭቶቹም ስረአቱን ብቻ ተጠያቂ የሚያደርጉ ሰዎች እየተበራከቱ መጥተዋል። ከፊሎቹ (ጎራ 1) የፌዴራል ስራቱን ከመጀመሪያውም ያልተቀበሉ ናቸው። ከፊሎቹም (ጎራ 2) ደግሞ የግጭቶቹ አይነትና መጠን እየከፋና እየጨመረ በመጣ ቁጥር ሁኔታው ስላስፈራቸው አቋማቸውን በሂደት *ያስተካከሉ* ናቸው።

እንደኔ እምነት ፌደራላዊ አስተዳደሩን እንደ ስረአት ባጠቃላይ ተጠያቂ ከማድረግ ይልቅ፤ ወያኔ በቀጥታ ከሚያካሄደው ሴራ በተጨማሬ የክልሎች አወቃቀር በራሱ ለግጭቱ መፈጠር ምክኒያት ሊሆን እንደሚችልም ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ያስፈልጋል ባይ ነኝ (ጎራ 3)። አወቃቀሩ ቋንቋ ላይ ብቻ የተመሰረተና የብሄርን ሃረግ ተከትሎ (አንቀጽ 46) የሚሄድ በመሆኑ አወቃቀሩ በሶማሌና በኦሮሞ ወሰን ላይ ለተፈጠሩት ግጭቶች የራሱን አስተዋጾ አድርጓል የሚል እምነት አለኝ። ላላለፉት ግጭቶች ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱም በየክልሎች ወሰን መሃልም ሆነ በክልሎችም ውስጥ ሊነሱ ለሚችሉ ግጭት የተዳፈነ እሳት ወይም የተቀበረ ፈንጂ ሊሆን ይችላል የሚል ፍርሃቻም አለኝ። በሌላ ጎራ (ጎራ 4) ያለው ደግሞ የፈዴራሉ ህገ መንግስት በትክክል ስራ ላይ ያለመዋሉ እንደትልቅ ችግር አድርጎ ከማቅረብ ውጪ ህጉ ይሄ ይጎድለዋል ወይም ይሄ ይሻሻል ሲሉ የማይሰሙ ቡድኖችና ግለሰቦች አሉ። በዚህ ጎራ ውስጥ ያሉ ሰዎች ህገመንግስቱን እንዲሁም በውስጡ ያካተተውን ስለክልሎች የሚናገረውን አንቀጽ (አንቀጽ 46) እንደማይቃወሙ ነው የምገነዘበው። በዚህ ጎራ ያሉ ሰዎች ህጉ ለብሄሮች መብት ስጥቷል፣ የብሄሮች ማንነት (identity) አሳድጓል፤ በኢትዮጲያ ህዝቦች መሃል ያለውንም ግኑኝነት አሻሽሏል ነው የሚሉት። እኔም ለብሄሮች መብት መስጠቱንና የብሄሮችን ማንነት ማሳደጉን አልክድም። በኢትዮጵያ ህዝቦች መሃል ያለውን ግኑኝነት አሻሽሎታል የሚለውን አባባል ግን ውሃ የሚቋጥር ማረጋገጫ አለው ብዩ ለመቀበል ያስቸግራኛል። በኦሮሞና በአማራ መካከል ለተፈጠረው መቀራረብ ወያኔ በሁለቱ ህዝቦች ላይ እያደረስ ባለው ግፍ የተሞላበት አገዛዝ የተነሳ የተፈጠረ መተሳሰር/ሶሊዳሪቲ ነው። በሁለቱ ህዝቦች መሃል ያለው ታሪካዊ ግንኙነትና የደም መተሳሰሩም መረሳት የለበትም። በቅርቡ ደግሞ እንደለማ መርጌሳ ያሉ ቆራጦች ከወያኔ ፍላጎት ውጪ ተንቀሳቅሰው ያስገኙት ውጤት የሁለቱ ህዝቦችን ግንኙነት አዲስ ምእራፍ ላይ በማድረሱ ነው። እንግዲህ በሁለቱ ህዝቦች መሃል እየተሻሻለ ለመጣው ግንኙነት የነኚህ ሁሉ ድምር ውጤት እንጂ የፌዴራል ስረአቱ ያመጣው አይደለም። እንዳውም ክልሎችን የማዋቀሩ ስራ የዘርን/የብሄርን መስመር ተከትሎ ስለሄደ በርግጥ የራስን ብሄር አንድነት ሊያጠናክር ችላል። ግን ብሄሮች/ህዝቦች ከሌላው ህዝቦች/ብሄሮች ጋራ ያለቸውን ግኑኝነት እንዳላላው/እንዳዳከመው የማይካድ ሃቅ ነው። በፊትም በህዝቦች መሃል ግንኙነት አልነበረም ብለው የሚናገሩ እንዳሉ አውቃለሁ፣ እነሱን ግን ምንም ማድረግ አይቻልም።

ሕገመንግስቱ ክልሎች የሚዋቀሩት በህዝብ አሰፋፈር፣ ቋንቋ ማንነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ነው ቢልም በተግባር ሲመነዘር ግን የብሄርን ሃረግ ተከትሎ የተሰራ የክልል አወቃቀር ነው የሆነው። የህዝብ አሰፋፈር የሚለው መስፈርት በስራ ላይ ሲውል አይታይም። በሃረሪ ክልል ውስጥ የሃረሪ ብሄር (7%) ኦሮሞው (52%) አማራው (32%) ነው። ጉራጌው፣ ሶምሊው፣ ትግሬው እና አርቦጋው ዝቅተኛውን ድርሻ ይዘው ይከተላሉ። የክልሉ አወቃቀር ግን የህዝቦችን ስብጥር በፍጹም አያሳይም፤ የህዝብ አሰፋፈር የሚለው መስፈርት ቦታ የለውም። ባለፉት 26 አመታት የታየው የብሄርን መስመር ተከትሎ የሄደው የክልሎች አወቃቀር ብሄርተኝነትን እያሳደገ ሲሄድና በህዝቦች መሃል ያለውን (ኢቶዮጲዊነት) እያኮሰሰው እንደሄደ ነው። በክልሎችም መሃል እየተደጋገመ ለተከሰተው ግጭት ዋነኛውም ባይሆን አንዱ ምክኒያት ይሄው ነው ማለት ይቻላል። ጥያቄው ከውዲሁ ካልታፈታ ለወደፊትም በየክልሉ ውስጥ በሚኖሩ ህዝቦች መሃልም ግጭት ይቀሰቅሳል የሚል ፍራቻ አለኝ። በመሬት ውስጥም እንደተቀበረ ፈንጂ ነው የማየው። የጽሁፌም አንደኛው አላማ በኢትዮጵያና በሌላ አገሮች (ስዊስ)

መሃል ክልሎችን ማዋቀር በተመለከተ ያለውን መሰረታዊ የአወቃቀር ልዩነቶች መኖሩን ለማሳየት ነው። ለምን በሃገራችን ባሉ ክልሎች መሃልና በክልሎችም ውስጥ ግጭት ይፈጠራል? ግጭቱ ክልሎች የተዋቀሩበት መስፈርት ያስከተለው ችግር ነው? የስዊስን ተሞክሮ ካገራችን ጋራ በማነጻጸር ለጥያቄዎቹ/ችግሮቹ መልስ ሊሆን የሚችል ግንዛቤ ለማስጨበጥ ነው። ችግሩን ማስየቱ የመፍትሄው አካል በመሆኑ ችግሩን ለመቅረፍ ከተቻለም ለማስወገድ ለሚቀርቡ ውይይቶች አስተውጽ እንዲኖረው በማሰብ ነው።

ሑለተኛው አላማዬ ብሄሮችን በሚመለከት በህገ መንግስቱ ላይ የሰፈረውን የመንግጠልን ጥያቄ መዳሰስ ይሆናል። ህገመንግስቱ በብዙ እጁ ለብሄሮች መብት ተገቢውን ምላሽ የሚሰጥ መሆኑን ላሰምርበት እፈልጋለሁ። ችግር ሆኖ የማገኘው የመገንጠልንም መብት በህገመንግስቱ ውስጥ ሲካተት ነው። እንደኔ አስተያየት ይህ አንቀጽ ህገ መንግስቱ ላይ መስፈሩ ወደጫፍ የሄደ (እክስትሪምዝም) ነው ባይ ነኝ። የመገንጠልን መብት በህገመንግስቱ ላይ ያካተተ አንድም የአፍሪካ አገር ያለ አይመስለኝም።የዲሞክራሲ ባህል ባደገባቸው አገር ውስጥም እንዲሁ። እኔ እስከማውቀውና እስከማስታውሰው ድረስ የመገንጠልን መብት በህገ መንግስቱ ውስጥ ያካተተ የዱሮው ሶቪየት ይመስለኛል፤ ሌሎች መኖራቸውን አላውቅም። ግንዛቤ ለማስጨበጥ ያህል ግን የመሰለኝን መሰረታዊ የታሪክ ማስረጃ ከወዲሁ ለማቅረብ እሞክራለሁ። በሺ ዘጠኝ መቶ አስራ ሰባት አመተምህረት፣ ከዛሬ መቶ አመት በፊት የሩሲያ ህዝቦችን መብት የሚገልጽ ዶኩመንት በቦልሼቪኮች የተረቀቀ ሰነድ ነበር። በራሺያ ውስጥ ያሉ ህዝቦች የመገንጠልም መብት እንዳላቸው በሰንዱ ውስጥ ተካቶ ነበር፤ በመጨረሻም ህገ መንግስት ሆኖ የጸደቀ ይመስለኛል። ይህ መብት በዛሬዋ ራሺያ ህገመንግስት ውስጥ ይኑር፤ ይሰረዝ የማውቀው ነገር የለም። ከአርባ አመት በፊት የማውቀውን ነገር ለማስታወስ ሞከርኩ እንጂ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ ነኝ ለማለት አልችልም። እንግዲህ ይህ መብት ነው በኢትዮጵያ ህገ መንግስት ውስጥ ስር የሰፈረው። የመገንጠል መብት በህገ መንግስቱ ውስጥ መካተቱ ምናልባትም ባገሪቱ ላይ እየተደረገ ያለ አደገኛ እክስፐሪመንት ነው ለማለት ይቻላል።

ስለ ኢቲዮጲያ ብሄሮች መብት ሰናወራ ወድኋላ ሄደን ትንሽ ታሪክን መቃኘቱ አይከፍም። የትናንቱን ታሪክ መመልከቱ ከዛሬው ተጨባጭ ሁኔታ ጋራ ለማወዳደር ያመቻል። ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ የሚውል ሳይሆን ግልጽና ተጨባጭ መልስም ለማግኘት ይረዳል። ስለሆነም ዛሬ በመሬት ላይ ወርዶ በኢቲዮጵያ የሚታየው የፖሊቲካ ሃቅ ምንድነው ብሎ መፈተሽም አስፈላጊ ይሆናል።

**የፌደራሊዝም አስተዳደር አስተማምኝነት**

በውነቱ በኢቲዮጵያ ታሪክ ውሥጥ ብሄሮች መብታቸውን ተከብሮላቸው ይኖሩ ነበር ማለት አይችልም። በተወለዱበት አካባቢ (ክልል) እንኳን በቋንቋዋቸው የመማርና የማስተማር እድል አልነበራቸውም። የፍርድቤቱም ችሎት ሆነ በመንግስት ድርጅቶች ውስጥም ያሉ ግልጋሎቶች በቋንቋቸው ስለማይተገበሩ ጉዳያቸውን የሚያስፈጽሙት ባስተርጓሚ ነበር። ይሄ የትላንትናው ታሪክ ነው። የትላንት ወዲያው ፣ ማለት ከደርግ በፊት የነበረው ደግሞ በብሄሮች ላይ ይደርስ የነበረው የ ኮኖሚ በደል ጭምር እንደነበር ነው። በነበረው የመሬት ሰሪት የተነሳ በደቡብ የኢትዮያ ህዝብ/ብሄሮች ላይ የከፋ የኢኮኖሚ በደል ይደርስ ነበር። ገበሬው ካመረተው ምርት እስከ ሁለት ሶስተኛውን ለባላባቶቹ ይከፍልም ነበር። ባላባቶች ሲባል በአካባቢው የሚኖሩትንና ከአካባቢው እርቀው (absentee landlords) የሚገኙትን፤ አማራም አማራም ያሎሆኑ ያካተተ ማለት ነው። ይህንን ደግሞ በእኔ እድሜ ክልል ውስጥ የምንገኝ ሰዎች ያየነውና የምንመሰክረው ነገር ነው።

በንጉሱ ጊዜ የነበረውም የመሬት ስሪት ከዓርባ አመት በፊት ተሽሯል፤ ባለፉት ሃያ ስድት አመት ውስጥም የብሄሮቿን መብት በተመለከተ እጅግ የሆነ መሻሽል ታይቷል። እነኚህን መብቶች በሚያስተማምን ሁኔታ ቀጣይነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ፌደራላዊ ስርአቱ ብቸኛ አማራጭ ነው ተብሎም ሲሰራበት ሃያ ስድስት አመት አልፎታል። ችግሩ ሕገመንግስቱ በሚገባ ስራ ላይ ባለመዋሉ እንጂ ፌዴራላዊ አስተዳደር ብቸኛ አማራጭ ነው የሚል ጠንካራ አመለካከትም ያላቸው ይገኛሉ (ጎራ 4)። በጽንሰ ሃሳብ ደረጃ ፌደርሊዝም በተዋረድ የስልጣን ክፍፍል ስለሚያደርግ የብሄሮችን/የህዝቦችን መብት ለማስከብር ጥሩ አማራጭ መሆኑን በግሌ ብቀበልም <u>ብቸኛ አማራጭ</u> ነው ብዬ ለማመን ግን ያስቸግረኛል። በአለም ላይ ብዙ አብላጫ ቁጥር ያላቸው አገሮች አሃዳዊ ስርአትን የሚከተሉ ናቸው። ከነዚህ መሃል ደግሞ ከፊሎቹ የዲሞክራሲ ባህላቸውና ተሞክሮዓቸው በላቀ ደርጃ ላይ የሚገኝ ነው። የግለ ሰብ መብትና የህግ የበላይነትን ማእከል ባደረገ የዲሞክራሲ ጽንሰ ሃሳብ ላይ የቆመ ስረአትን ፈጥረው የሚተዳደሩ ናቸው። በረጂናልና በሎካል ደረጃ ላሉ አስተዳደሮችም መብትን በተመለከተ ብዙ ርቀት ይሄዳሉ ( Decentralisation)። እስከ አውቶኖሚ የሚደርስ ካለዛም ወዳአውቶኖሚ የሚጠጋ መብትም ይሰጣሉ። በነዚህ አገሮች ብዙውን ጊዜ በህዝቦቻቸው መሃከል የሚነሱ ልዩነቶች የሚፈቱት በውይይት ቢሆንም፤ አልፎ አልፎ ግን በጉልበት ለመፍታት የተሞከረበትም ጊዜ ታይቷል። በደሞክራሲ የማይተዳደሩ የአሃድያን አገሮች ታሪክ ግን ሌላ ነው፣ ስለነሱ መተረኩም ፋይዳ የለውም።

የህዝቦች/ብሄሮች መብት አስተማማኝ ሆኖ እንዲቀጥል ሁሉም ህዝቦች የተስማሙበት የስልጣን ክፍፍል መደረግ አለበት። ህብረቱ ውስጥ ባሉ ህዝቦችና ህብረቱን በበላይ ሆኖ በሚመራው መአከላዊ መንግስት መካከል የጋራ ስምምነት መኖር ይኖርበታል። ህዝቦች በራሳቸው ክልል ራስን የማስተዳደር መብት ይኖራቸዋል፤ የመአከለኛውም መንግስት ደግሞ ከፍተኛውን የሃላፊነት ስልጣን ወስዶ የፌዴራል ሰራአቱ ዋና አስተዳዳሬ ይሆናል። በህግ ተደንግጎ በተቀመጠ ደንብ መሰረት ክልሎች የራሳቸው ብቻ የሆነና እንዲሁም ከማእከላዊ መንግስት ጋራም የሚጋሩት ስልጣን ይኖራቸዋል። ከዚህም የተነሳ በዚህ ስራት ውስጥ የሚኖሩ ህዝቦች/ብሄሮች የስልጣን ተቋዳሽ ይሆናሉ፣ ተገልለናል የሚል ስሜታቸውንም በጅጉ ይቀነሳል።

በኢቲዮጲያ የሚታየው ግን የያንዳንዱን ክልል ፖሊቲካዊ፤ ድርጅታዊና ኤኮኖሚያዊ ህይወት በወያኔ ሲመራ ነው። ይህንን በመቃወም ዛሬ ክልሎች ተነስተው ራሳችንን በራሳችን የማስተዳደር ሀገ መንግሥታዊ መብታችን ይጠበቅ፣ የወያኔ በክልላችን የፖሊቲካ፤ የድርጅትና የኤኮኖሚያዊ ህይወት ገብቶ ማዘዙ ይቁም በማለት እየተነሱ ናቸው። መብታቸውን ለማስጠበቅ እንደገና ሌላ ትግል እያደረጉ ናቸው ማለት ነው።

**ፌደራላዊ አስተዳደሩ**

ህገመንግስቱ በሚረቀቅበት ጊዜም ሆነ በማጽደቁም ላይ በነበረው ሂደት ላይ ተሳትፎው የነበረው ደርግን አስወግደው ስልጣን በጨበጡት የብሄር ድርጅቶች ዙሪያ ብቻ ነበር። ከአመራሮቹና (ከፖሊቲካል ኤሊቱና) ካንዳንድ ደጋፊዎቻቸው በስተቀር ህዝቡ ተሳትፎ አልነበረውም። ይሄ ከመጀመሪያውም የፌደራሉን ስርአት ታማኝነት ጥያቄ ውስጥ እንዲገባ አድርጎታል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በድንበር ማካለል በሚል ምክኒያት በኢቲዮጵያ ሶማሊዎችና በኦሮሞ ህዝቦች መካከል በተነሳው ግጭት ትልቅ የህዝቦች እልቂትና መፈናቀል ደርሷል። የኢቲዮጲያን ህዝብ ልብ ስብሮ ሃዘነተኛ አድርጎታል፤ የሃዘኑም ድንኳን ገና አልፈረሰም፤ ሃዘነተኞቹም አልተሰናበቱም። ባጭሩ በዘመናች አይተነውም ሰምተነውም የማንውቀው ነገር ነው ተከስቶ ያየነው።

ስለግጭቱ ብዙ መሰረታዊ ምክንያቶችንና ሰበቦችን መደርደር ይቻላል። ወያኔ በግጭቱ ላይ ያለው ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ አንደኛውና ዋናው ምክኒያት ግን ድምበር ማካለልን ተመልከቶ የተነሳው ግጭት መሆኑ ግልጽ ነው። ቋንቋንና ብሄርን መሃል አድርጎ በተካለለ ክልል ውስጥ ሃያ ሰባት አመት የኖሩ ህዝቦች ከዜግነት ይልቅ ብሄሬ የሚለውን አስተሳሰብ ያዳበረ ትውልድ እንዲያፈሩ አድርጓቸዋል። ለኔ ይገባል ላንተ አይገባም በሚል ንትርክ ውስጥም ተጠምደዋል። ሶምሊያ በኦጋዴን ላይ የነበራትን የይገባኛል ጥያቄ አንስቼ አንድ ምሳሌ ላቅርብ። ኦጋዴንን ገንጥሎ የታላቋ ሶምሌ አካል ለማደረግ በተደረገው የረጅም ጊዜ የጦርነት ታሪክ ውስጥ ዛሬም ቢሆን የሃሳቡ አቀንቃኞችና ነፍጥም አንግተው የሚዋጉ እንዳሉ መርሳት የለብንም። አብዲሌና በአካባቢው ያሉ ሰዎችም ያስተሳሰቡ ተሸካሚ ሊሆኑ አይችሉም ብሎ መናገር ያስቸግራል። እንግዲህ ይህ አይነት አስተሳሰብ ያላቸው ግለሰቦችና ቡድኖች ክልላቸውን በማይታይ ግንብ ያጥራሉ፤ አስተሳሰባቸውም "ታላቋም ሶምሊ" በሚል ምኞት ስለተመሰረተ በሌሎች ክልል ውስጥ ያሉ ግዛቶችንም ይጨምራል፤ በክልሎች መሀል ለሚፈጠር ግጭትም ምክኒያት ይሆናል ማለት ነው። በሌሎች ክልሎች ሌላውን የማግለልና የራስን ማሳደግ ፍላጎት የለም ማለት አይደለም።

በሌሎች ክልልም ባሉ ህዝቦች መሃል የምናየውም ግጭት የዚሁ አካል ነ።. እንግዲህ ይሄንን የተመለከተ ሰው ፌደርላዊን ሰራት ጥያቄው ውስጥ ማስገባት ቢጀምር የሚገርም አይሆንም። አሃዳዊ ሰራትንም እንደአማራጭ ቢወስድም ቅን ልቦና ከፈጠረው አስተሳሰብ የመነጨም ሊሆን እንደሚችል መገንዘብ ያስፈልጋል። የዱሮ ስራአት ናፋቂዎች ብሎ ማጥላላቱ ተገቢ አይሆንም። ቁምነገሩ በየክልሎቹ መሃል የሚፈጠሩ ግጭቶችን ለመቅረፍ ከተቻለም ለማጥፋት ውይይት መክፈቱና የሑሉንም ሓሳብ መሰማቱ ነው። ውይይቱ ግን ግጭቱን ምክንያት አድርጎ ሌላውን የብሄሮች መብት የሚያፋልስ መሆን የለበትም። በግሌ የፈደራላዊውን ሰርአት እንደ መጀመሪያ አማራጭ የምቀበል ብሆንም፣ ምርጫዬ ግን የተመሰረተው ስለፌደራል ሰርአት በጥናት ላይ ያተመሰረተ በቂ እውቀት ኖሮኝ አይደለም።

መረሳት የሌለበት ነገር የፌደራሊዝምን አስተዳደር በኢትዮጵያ ውስጥ ያስገቡት በብሄር ተደራጅተው ዛሬ ስልጣን የጨበጡት መሆናቸውን ነው። ከመጀሪያውም አነሳሳቸው መብታችን አልተከበረም የሚል ነበር። ስለዚህም ነፍጥ አንስተው ለብዙ አመት ታገሉ በመጨረሻም ለድል በቁ። ከዚህ በኋላ ማንም ሰው እንደሚጠብቀው የብሄሮችን መብት የሚያስከብር ስረአት አወጁ ፣ የፌደራል አስተዳደርንም ዘረጉ። በእዚህ ሰርአት ውስጥ ተወልዶ ያደገው ዛሬ ጎልማሳ ሆኗል። ፈደራሊዝሙ ያመጣላትን መብት እያየና እየዳሰሰ አድጓል። ለምሳሌ ያህል በመንግስታዊ ድርጅቶችና በፍርድቤቶችም ጉዳዩን በራሱ ቋንቋ ሲያስፈጽም፤. በትምህርትቤትም በራሱ ቋንቋ ሲማርና ሲያስተምር ነው ያደገው። በክልሉ አስተዳደር ደግሞ የክልሉን ህግ የማውጣት፣የኢኮኖሚ ፖሊሲ መቀየስ፣ ታክስ መጣል፣ ፖሊስ ማደራጀትና መምራት የሚሉ መብቶች ተሰጥቶታል፤ መብቱም በስራ የተተረጎመው በፈደራላዊ ሰርአቱ እንደሆነ ያውቃል። እንግዲህ ለእንደዚህ አይነቱን ህብረተሰብ በምን ተአምር ነው የአሃዳዊ ሰርአት እንደሚሻል ማስረዳት የሚቻለው። ከምታየው የምትሰማውን እመን እንደማለት ይሆናል።

በክልሎች መሃል ያለው ግጭት እና መፈናቀል ቢቀጥልም እንኳን ማሳመን ያስቸግራል። በመሰለኝ መንገድ የራሴን ሎጂክ ደረደርኩ እንጂ የአሃዳዊ ሰረአት አቀንቃኞች ማሳመኛ የመከራከሪያ ነጥብ የላቸውም ብዬ ድምዳሜ ላይ መድረሴ አይደለም።

ሌላው ደግሞ በእውነተኛ ፌደራላዊ ህገ ደምብ መሰረት በክልሎች ሰልጣን ውስጥ ጣልቃ መግባት አይቻልም። በአሃዳዊ ሰረአት ግን መንግስት በረጂናልና በሎካል አስተዳደር ውስት እንደማይገባ እርግጠኛ መሆን አይቻልም። ለምሳሌ እኔ የምኖርበት ሃገር ዲሞክራሲያዊ ባህል የዳበረበት ግን በአሃዳዊ ሰረአት የሚተዳድር ነው። ይሁን እንጂ መንግስት በሎካል (municipalities- kommuner) አስተዳደር ደርጃ ወርዶ ያቀዱትን ስራ ውስን የማድረግና ከዛም አልፎ የመሰረዝ ሙሉ የህግ መብት አለው። በፌደራል ስረአት ውስጥ ግን ድርጊቱ ህጋዊ ችግርን ስለሚፈጥር የማይቻል ነገር ይሆናል። (የእቲዮጵያን ፈደራሊዝም ግን አይመለከትም)

**የክልሎችን ግጭት ከመቅረፍና ከማስቆም አንጻር ፣ ሃሳብ**

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረሥ ክልሎች ያለማእከልዊው መንግስት ጣልቃ ገብነት ራሳቸውን የማስተዳደር ሙሉ መብት አልነበራቸውም። በየቦታው ባሉ ክልሎቹ ውስጥ በአስተዳደሩ ላይ የተቀመጡት አመራሮች የወያኔ ስራ አስፈጻሚ እንጂ የወከላቸውን ህዝብ ጥቅምና ፍላጎት የሚያስከብሩ አይመስሉም ነበር። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በዚህ አይነቱ ሁኔታ ስር ሆኖ መገዛት የመረረው ህዝብ በፊልት ለፊት ወጥቶ ራሴን በራሴ ላስተዳድር እያለ የወያኔን የበላይነት በመቃወም የመረረ ትግል እያካሄደ ነው። ከወያኔ ጋር ከሚደረገው ትግል በተጨማሪም በክልሎችም መሃል በይገባኛል ምክንያትና በወያኔም ተንኮል የተነሳ ብዙ ደም መፋሰስና መፈናቀልም እየተከሰተ ነው። ብዙ ጊዜ እንደሚባለው በክልሎች መሃል ለሚፈጠረው ግጭት ዋናው ምክንያቱ ወያኔ ነው የሚል ነው። ለከብት ግጦሽና ውሃ ፍለጋ ከቦታ ቦታ መዘዋውሩም ሌላው ምክንያት እንደሆነ ይገለጻል። ምክንያቶቹ ብዙዎችን የሚያስማሙ ናቸው፤ ሆኖም ብዙ ጊዙ በቂ ትኩረት የማይሰጠው ህገ መንግስቱም አስተዋጽኦ ማድረግ መቻሉን ነው።

ሕገመንግስቱ ክልሎች የሚዋቀሩት በህዝብ አሰፋፈር፣ ቋንቋ ማንነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ ነው ቢልም በተግባር ሲመነዘር <u>ቋንቋን ብቻ</u> ማከላዊ አድርጎ የሚፈጠር የክልል አወቃቀር ሆኖ ይገኛል። ይሄ ደግሞ የዘር መስመርን ተከትሎ አንድ ቋንቋ የሚናገሩ ህዝቦችን በአንድ ላይ ተጠቃለው በአንድ ክልል ስር አንድ አስተዳደር እንዲመሰርቱ አድርጓቸዋል። ህዝቦች በጥቂት ሜትር ርቀት ላይ ከሚገኘው የሌላ ብሄር አባል ከሆነው ይልቅ በብዙ ኪሎሜትሮች ርቀት ላይ ከሚገኘው የብሄራቸው አባል ጋር ያለውን ትሥስር ማጠናከር ሆኗል። ትሥስሩን ማጠናከሩ በራሱ መልካም ነው፤ ግን ይህ አይነቱ ትሥስር የብሄርተኝነትን እያሳደገ የዜግነትን አስተሳሰብ እያዳከመ ነው፣ እየታየም ያለው ይሄው ነው። የራስን ክልል ለማስፋት ሲባል የህዝብ ደም ይፈሳል ከመኖሪያውም ይፈናቀላል። ሁለት የተላያዩ አገሮች እንደሚያረጉት ጦርነት አይነት ማለት ነው። እየተናገርኩ ያለሁት ትልልቅ የመሬት ስፋት (የቆዳ ስፋት) ያላቸው ብሄሮች የያዙትን የቆዳ ስፋት መልቀቅ ወይም ማሳነስ አለባቸው አይደለም። ዓከላለሉ ቢያንስ ጂኦግራፊንም ቋንቋንም የህዝብንም ስብጥር መአከል አድርጎ ለአስተዳደር የሚያመች ሆኖ ቢነሳ ይበጃል ነው የምለው።

በርግጥ አባባሌ ዛሬ ባለው የክልሎች አሸናሸንና አስተዳደር ላይ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። አንድ የነበረው ክልል ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ሊሸነሸን ይችላል። ክልሎቹም ቋንቋቸውን እንደያዙ ቢቆዩም አንድ አስተዳደር ግን አይኖራቸውም። እንደ ክልሎቹ የመሸንሸን ብዛት የአስተዳደሩ መጠንም ይወሰናል። ለምሳሌ የኢቲዮጲያ ሶማሌ ክልል ሁለት ቦታ ቢሸነሸን ሁለት ክልሎችና (states) ሁለት የክልሎች አስተዳደሮች ይኖሩታል ማለት ነው። ክልሎቹ መብታቸውን እንደያዙ ሆነው አግዳሚ ግኑኝነትም (horizontal relation) ማድረግ ይችላሉ። በሃላዊና ኢኮኖሚያዊ እንዲሁም የክልሉ ህግ በሚፈቅደው መሰረት ሌላም ግንኙነት ከማድረግ አይታገዱም።

በአንዳንድ የፌዴራል አገሮች ውስጥም አንድ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ህዝቦች በብዙ ክልሎች ተከፋፍለው ይኖራሉ። ተከፋፍለው መኖራቸውም በቋንቋቸው ከመገልገልና ቋንቋቸውንም ከማዳበር ኣላገዳቸውም። በማህላቸው ሊኖር የሚችለውን አግዳሚ ግኑኙነቱንም (horizontal relations) አልቀነሰውም። ለምሳሌ በስዊዘርላንድ የፌዴራል ስራዓት ውስጥ ሃያ ስድስት ስቴቶች (cantons) አሉ። አራት ብሄራዊ ቋንቋዎችም ይነገራሉ። በየስቴቶቹ ያለው የህዝብ ብዛትም በጣም ይለያይል። ከነኚህ መሃል ስድሳ ሶስት በመቶ የሚሆነው ጀርመንኛ ተናጋሪ ሲሆን፤ ቋንቋውም ከሃያ ስድስት ስቴቶች በአስራ ሰባቱ ውስጥ ብቸኛው የመገልገያ ቋንቋ ነው። በአስራ ስባቱም ስቴቶች (ክልሎች) ውስጥ ጀርመንኛ ተናጋሪው ባስራ ሰባት የአስተዳደር ክልሎች ተሸንሽኖ ይገኛል። በተጨማሪም በአራት ክልሎችም ውስጥ ከቀሩት ሶስት ቋንቋዎች ጋር አብሮ ይነገራል። ለምሳሌ ጀርመንኛ ከሌላ ቋንቋ ጋር አብሮ ከሚነግርባቸው ስቴቶች መሃል አንዱ የፍሪቡርግ ስቴት (fribourg canton) ነው። በዚህ ስቴት ውስጥ ፈረንሳይኛ ተናጋሪው በምራብ፣ ጀርመንኛ ተናጋሪው በምስራቁ ፍሪቡርግ ውስጥ ይኖራሉ። በስቴቱ ውስጥ

ሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ከተሞችም (billingual towns) አሉ፤ በመኖራቸውም የተላያዩ ኢንቬስትሜንቶችን የመሳብ (attract) ችሎታም ተፈጥሮላቸዋል።

ሌላው ምሳሌ ግሪሶን ተብሎ በሚጠራው ስቴት (Grison canton) ውስጥ ጀርመንኛ (73%) ሮማንሽ (15%) ጣልያኒኛ (13%) ተናጋሪዎች ይገኛሉ፣ ሶስቱም ቋንቋዎች የስቴቱ የመገልገያ (official) ቋንቋዎች ናቸው። የስቴቱ (gison canton) ህግ መግቢያ (preamble) ላይ እንደሰፈረው የስቴቱ አላማ "ነጻነትን፣ ሰላምንና የሰውልጅ ክብርን (human dignity) ማስጠበቅ፣ የዲሞክራሲና የህግ በላይነትን ማረጋገጥ፣ ብልጽግናንና ሰብአዊ መብቶችን (social justice) ማሳደግ፣ በክልል ውስጥ ያሉትን ሶስት ቋንቋዎች ማሳደግና በውስጣቸው የሚገኘውን የተለያየ ባህላቸውንም (የሶስቱም) የታሪካቸው ውርስ በመሆኑ ከብካቤ ያስፍልገዋል" የሚል ነው። (ሰረዝ የተጨመረ)

የሁለቱን አገሮች ፌዴራል ስራት ለማመሳሰልና ለማወዳደር አስቸጋሪ እንድሚሆን ይገባኛል። በስዊስ ስቴቶች መሃል ያለውን ወሰንን የማካለልም ስራ ሲሰራ ትልቅ ቦታ የተሰጠው መስፈርት ቋንቋ ሳይሆን ሃይማኖታዊ (denominational consideration) ነው። በስዊስ የፌዴራል ስርአት ታሪካዊ አመጣጥም ከሃገራችን በጣም ይለያል። ከፌዴራሽኑ በፊት የተላያዩ ክልሎች (ካንቶንስ) የየራሳቸውን ሰራዊት፣ የየራሳቸው የሆነ ገንዘብ ኖሯቸው ራሳቸውን በነጻ የሚያስተዳድሩ ነበሩ። እነኚህ ክልሎች ናቸው ተሰባስበው ፌደራሽኑን የፈጠሩት።

ሆኖም የስዊስን ተሞክሮ መመልከትና ከሃገራችን ተሞክሮ ጋራ ማመዛዘን ይቻላልም ጠቃሚም ነው ባይ ነኝ። ጀርመንኛና የፈረንሳይ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ህዝቦች አብረው ባንድ ስቴት- ክልል (fribourg canton) ውስጥ ሲኖሩ አይተናል፤ በሌላም ሁለት ስቴቶች ውስጥ አብረው ይኖራሉ. በግሪሶን ክልል (grison canton) ውስጥም ያሉ ሶስት የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩ ህዝቦች አብረው ይኖራሉ. ጀርማንኛ ቋንቋ ብቻ የሚነገርባቸውም ክልሎች (cantons) በብዙ ቦታ ተሸንሽነውም ይታያሉ. ህዝቦች አንድ ቋንቋ ስለሚናገሩ በአንድ ክልል ውስጥ አይኖሩም፣ የተለያየ ቋንቋ ስለሚናገሩ በተለያየ ክልል ውስጥ አይኖሩም. እንዳውም የተለያዩ ህዝቦች በአንድ አስተዳደራዊ ክልል እየኖሩ ባህላቸውንና ቋንቋቸውን የማሳደግና ባህላቸውንም ጠብቀው ለማኖር እንዴት እንደሚተባበሩ የግሪሶን ስቴት ህግ ጥሩ ምሳሌ ነው።

ከስዊስ ተሞክሮ ስነሳ ቋንቋን ብቻ መሰረት አድርጎ ባልተፈጠረ ክልል ውስጥ የህዝቦች ግጭት እንደማይታይ ነው የምረዳው። በተቃራኒው ባገራችን በአዋሳኝ ክልሎች መሃል ግን ግጭት ማየቱ የተለመደ እንደሆነ ነው። ባገራችን በቋንቋና በብሄር ልዩነት የተነሳ ህዝቦች ከክልሎች ሲባረሩ ብዙ ጊዜ አይተናል። የኢቲዮጵያን ችግር አነሳሁ የስዊስን ስኬታማነትንም በትንሹም ቢሆን ለማቅረብ ሞከርኩ። አስቀድሜ ከላይ እንደገለጥኩት አላማዬ በኢትዮጲያ የክልል አወቃቀሩ ለግጭቶች ምክኒያት ሊሆን ይችላል ብዬ ስለምገምት ግጭቶችን ከማስቀም አንጻር የክልሎችን አወቃቀር እንዲሻሻል የውይይት ሃሳብ ማቅረቤ ነው። ችግሩ ከወዲሁ ካልተፈታ ለወደፊቱ የባሰ ግጭት ሊያስነሳ ይችላል የሚል ፍርሃቻም አለኝ። በክልሎች መሃል ብቻ ሳይሆን በክልሎችም ውስጥ ሊከሰት የሚችል አደጋ ይመስለኛል። ውይይቱ ስኬታማ እንዲሆን አስተማማኝ የሆነ ድምዳሜ ላይም ለመድረስ እንዲቻል የብዙ አገሮችን ተሞክሮ መመልከትና በጥያቄው ዙሪያም ምርምርም ያደረጉ ግለሰቦች ወደፊት መጥተው ሃሳባቸውን ቢያሰሙ ይመረጣል።

**መገንጠልን ያካተተው መብት አንቀጽ (39)**

የብሄር ጥያቄ ውይይትና ክርክር ሲደረግበት አንድ ትውልድ አልፎ ወደ ሁለተኛ ትውልድ የተደረሰበት ጊዜ ላይ ቢደርስም ውይይቱ አሁንም ብቅ ጥልቅ እያለ ቀጥሏል። የመገንጠልን ጥያቄ የተማሪው ንቅናቄ ከአርባ አመት በፊት መደገፉ ስህተት ነበር ብሎ ዛሬም ወቀሳ ማቅረቡ አላቆመም፣ ስህተት አልነበረምም ብሎ ክርክር መክፈቱ የትም አያደርሰም። ያኔም ቢሆን ጥያቄው የተማሪውን ንቅናቄ ሁለት ቦታ የከፋፈለ ነው። የማይገባኝ ግን ጥያቄውን ለመደገፍ ምክኒያት ነበር የሚባለውን ጭቆና ለማስረዳት ውይይት ሲጀመር የሚታየው ፍጥጫ ነው። በአጼም ከዛም ቀጥሎ እስከ ደርግ መንግስት ድረሥ የብሄሮች መብት ተረግጠው መኖራቸውን ለመካድ ወይም ላለመቀበል ያለውን ዝንባሌ ሳይ ነው። ያ ታሪክ ሆኗል እሱ ላይ አንረባረብ ወደፊት እንራመድ ማለት አንድ ነገር ሆኖ ሳለ ወደ ክህደት ለመሄድ መሞከሩ ቅንነት የጎደለው ነው ያስብላል፣ በህዝቦች መሃል መፈጠር አለበት የምንለውንም አንድነት ይጎዳል።

ሌላው ሊገባኝ የማይችለው ደግሞ የመገንጠል መብትን በዘመኑ ስንደግፍ ጊዜና ሁኔታ የማይለውጠው ዘላለማዊ የሆነ ግኡዝ እንደሆነ ነገር ተደርጎ የሚነገረውን አስተያየት ስሠማ ነው። እስከማስታውሰው ድረስ ዱሮም ጥያቄውን ስንደግፍ አንዱም በዘመኑ የነበረውን የፊውዳሉን ስርአት ለመጣል የሚደረገውን ትግል ይረዳል ከሚል እምነት በመነሳትም ነበር። ስርአቱን ጥሎ የሶሺያሊዝምን ስርአት ለመመስረት በሚደረገው ትግል ውስጥም የብሄሮች ትግል ለመደቡ ትግል አገልጋይ (subordinate) ይሆናል፣ በሶሺያሊስም የብሄሮችም ጭቆና ይጠፋል የሚል አመለካከት ስለነበረ ነው። አሁንም በዚህ

አመለካከት አምንበታለሁ እያልኩ አይደለም። የመገንጥልን መብት ቲዎሪ ያራምድ የነበረወ ስታሊን ራሱ የተወለደባት ጆርጂያ የመግንጠልን ጥያቄ ስታነሳ ጊዜው ለብሄር ጥያቄ ቀዳሚነት አይሰጥም በሚል ምክንያት ትልቅ ጭፍጨፋ ነው በጆርጂያ ላይ ያካሔዴው። እንግዲህ ያኔም ቢሆን በዘመኑ በሚቀነቀነው በስታሊን ቴዎሪም ቢሆን የመገንጠሉ መብት ግኡዝ ያልሆነ ጊዜና ሁነታ የሚወስነው ነበር ማለት ነው።

ባገራችን የመገንጠልን መብት ያካተተው አንቀጽ 39 ብሄሮች ያለምንም ቅድመ ሁኔታ (unconditional) ተገንጥለው የራሳቸውን መንግስት ለማቋቋም እንደሚችሉ ይገልጻል። የመገንጠሉን ጥያቄ ተግባራዊ ለማድረግም ጥያቄው "በብሄሩ፣ በብሄረሰቡ ወይም በህዝቡ" የህግ አውጪ ምክርቤት ውስት ሁለት ሶስተኛ የድምጽ ድጋፍ ካገኘ ይበቃል። ከዛ በኋላ ያለው ጉዳይ ህዝበ ምርጫ ተደርጎ ህዝቡ/በሄሩ በሚስጠው ድምጽ ይቋጫል የሚል ነው። ይሄንን መብት በህግ ደረጃ ማስቀመጡ ለምን አስፈለገ? ምንስ ማለት ነው? በርግጥ በሁለት ህዝቦች መሃል በተነሳ ግጭት አብሮ ለመኖር የማይቻልበት ደረጃ ላይ ሲደረስ ፣ አማራጩ መጨራረስ ብቻ ሲሆን፣ የሰላሙ መንገድ ተሚጦ ሲያልቅ፣የመለያየቱ ጥያቄ ተነስቶ ያኔ እንዴት እንደሚሆን ይወሰናል። ከወዲሁ ግን የብሄሮች የመገንጠልን መብት በህገ መንግስቱ ላይ ማስፈሩ ወደፊት ለሚመጣ መከፋፈል መንገድ መጥረግ፣ ማመቻቸትና የመገንጠል አላማ ላላቸውም ማበረታች መስጠት ነው። በአገራችን የክልሎች አዋቃቀርን ተከትሎ ከተፈጠሩት ችግሮ ጋራ ሲታይ የመገንጠል መብቱን በህገ መንግስት ላይ ማስፈሩ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንደማለት ነው።

መብቱ በህግ ላይ መስፈሩ የሚያመጣውን ጠንቅ ለመገመት በሃገራችን ውስጥ የሃይል ሚዛኑ እንዴት እንደሚቀያየርና የአካባቢውን ፖሊቲካ (geopolitics) መቃኘት ጠቃሚ ይሆናል። የሃይል ሚዛኑ በቀላሉና ባጭር ጊዜ ውስጥ የሚለዋወጥ መሆኑን የቅርብ ታሪካችን ይመሰክራል። ንጉስ አይከሰስ ሰማይ አይታረስ እየተባለ የንጉሱ ትልቅነት የሚወደስበት ዘመን ነበር። የደርግም ሰራዊት ከጥቁር አፍርቃ አገሮች ውስጥ ሃያል እንደነበረ ይነገርለት ነበር። ሁሉቱም መንግስታት አለፉ፣ ወያኔም ተተካ፣ ኤሪትራም ከኢቲዮጲያ ተገንጥላ ነጻ አገር ሆነች። ይሄ ሁሉ የሆነው ከሃምሳ አመት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ ነው። ነገ ደግሞ የሃይል ሚዛኑ ተለውጦ፤ ለመገንጠል የሚፈልግ ሃይል ተጠናክሮ ስልጣን ላይ ቢወጣ አንቀጽ 39 በሚፈቅድለት መንገድ ሄዶ በቀላሉ ሊገነጠል ይችላል ማለት ነው። ወያኔም ራሱ ህጉን ተጠቅሞ ትግራይን ይዤ እገነጠላለሁ ሊልም ይችላል። አንድ ጊዜ የሆኑ የ አፍሪካ መሪዎች የኤርትራን መገንጠል አስመልክቶ ለቡትሩስ ቡትሩስ ጋሊ የመገንጠሉን ሃሳብ እንደሚቃወሙ ሲነግሩት፤ በዘመኑ ያገሪቱ መሪ የነበረው መለስ ዜናዊ እየደገፈ እናንተ ምን አገባችሁ የሚል መልስ ነው የሰጣቸው። ወደፊትም አንድ ብሄር እገነጠላለሁ ብሎ ቢነሳ፤ ህገ መንግስቱ ይፈቅድለታል እናንተ ምን አገባችሁ የሚል መልስ እንዳይሰጠንና ታሪክም እራሱን ደሞ እንዳያሳየን እመኛለሁ።

በምስራቅ አፍሪቃ አካአባቢ ያለው የሃይል አሰላለፍ የሚያሳየውም ሃያላን አገሮች የስትራተጂክ ጥቅማቸውን ለማስከበር የሚያደርጉትን ሩጫ ነው። ፈረንሳይ፣ አሜሪካ፣ ጃፓንና ቻይና በጂቡቲ ውስጥ የጦር ሰፈር ገንብተዋል። የሶማሊላንድ መንግስትም ለተባበሩት አረብ ኤሚሬት የጦር ሰፈር ለመስጠት ስምምነት ላይ ደርሷል። ግብጽ ደግሞ በኤሪትርያ (ሳዋ) ቱርክ በሱዳን (ሳርኩን) ላይ የጦር ሰፈር አስፍረዋል እየተባለ ይነገራል። ክነዚህ መሃል አንዳንዶቹ በተገኘው ቀዳዳ ሁሉ በመጠቀም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የኢቲዮጵያን ፖሊቲካ በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ የሚፈልጉ መኖራቸው አለመዘናግት ያስፈልጋል።